አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ትምህርት ቢሮ

CITY GOVERNMENT OF
ADDIS ABABA EDUCATION
BUREAU

ቁጥር
REF.NO አ1.1/904/አ28-40/49

ቀን
DATE 21/12/10

ለኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት

አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የተማሪ ቅበላ መመሪያን ስለመላክ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተማሪዎችን ቅበላ እና ዝውውር በተለይም ከአንድ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት፣ከአንድ አካባቢ ወደሌላ አካባቢ፣ ከአንድ የትምህርት መርሃ ግብር ወ ደሌላ መርሃ ግብር የሚያደርጉት ዝውውር የተሳለጠ መሆን እንዲችል በስሩ ባሉት ሁሉም የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተግባራዊ የሚሆን የተማሪ ቅበላ መመሪያ አውጥቷል፡፡ ስለሆነም ይህንን የተማሪ ቅበላ መመሪያ ቁጥር 004/2010 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን እየላክን በትምህርት ቤቶች ውስጥ በጥበቅ ዲሲፒሊን ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ እንዲሆን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ታቦር ገብረመድህን (ዶ/ር)
የትምርት ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ:-

- ለቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለኢኮቴ ምክ/ቢሮ ኃላፊ
- ለዘርፈ ብዙ ጉ/ ም/ቢሮ ኃላፊ
- ለስር/ት/ዝ/ት/ ዳይሬክቶሬት
- ለፈተና ዝ/አስ/ዳይሬክቶሬት
- ለኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
  ትምህርት ቢሮ


መለስ ዜናዊ፤ ለህዝብ የተፈጠረ፣ ለህዝብ የኖረ ለህዝብ የተሰዋ ታላቅ መሪ!!
ሌ ጋሲህ ይቀጥላል ራዕይህም በትውልዶች ትብብሉሽ ይሳካል!!

☎22-38-84 FAX 223888 ✉ 744 E-mail www.aaceb.gov.et

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ Addis Ababa – Ethiopia
ማሳሰቢያ ሁልጊዜ የማገናዘቢያ ቁጥሮችን የጉዳዩን ርዕስና የሚመለከተውን ክፍል ይጥቀሱ

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# ትምህርት ቢሮ

## የተማሪዎች ቅበላ መመሪያ ቁጥር 004/2010

ነሀሴ 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

መግቢያ

ትምህርት ለሰው ልጅ አስፈላጊና ለልማት ሁሉ መሠረት ነው፡፡ በተለይም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት(1987) አንቀጽ 36 እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሕጻናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 28 ዜጎች ከሕጻንነት ጀምሮ የመማር መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ (1986) አንቀጽ 2 የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ማለትም ለየት ያለ የትምህርት አቀራረብ የሚስፈልጋቸው ዜጎች እንደ ችሎታቸው እና ፍላጎታቸው የመማር መብት እንዳለቸው ያስቀምጣል፡፡

እያንዳንዱ ዜጋ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት ፣በትምህርትና ስልጠና ፖሊሲውና በተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን መሠረት ያለምንም ልዩነት የመማር መብት ያላቸው ቢሆንም በከተማችን ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ጀምሮ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት የትምህርት አገልግሎት ለማግኘት ሲያመለክቱ በምዝገባ ወቅት በሚያጋጥማቸው ችግር ምክንያት የትምህርት አገልግሎት በተገቢው አለማግኘታቸው፤

ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት፣ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ፣ ከአንድ የትምህርት መርሐ ግብር ወደ ሌላ የትምህርት መርሐ ግብር ለመዘዋወር ሲያመለክቱ የአፈጻጸም ችግሮች ስለሚያጋጥሟቸው ትምህርታቸውን በአግባቡ መቀጠል አለመቻላቸው ፤

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ አንቀጽ 3፣የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን እንዲሁም የትምህርት ሚኒስቴር የ1994 ዓ.ም. የትምህርት ስልጠና ፖሊሲና አተገባበሩ ሰነድ ከዚህ በፊት ይጠየቁ የነበሩ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ቀርተው ከአንደኛ እስከ ዐሥረኛ ክፍል ድረስ ያሉ ተማሪዎች ያለምንም ክፍያ በነጻ እንዲማሩ ቢወስንም በአንዳንድ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችና ወላጆች በተለያዩ ምክንያቶች ክፍያ እየተጠየቁና መክፈል ባለመቻላቸው ምክንያት በነፃ የመማር መብታቸው እየተጣሰ በመሆኑ፤

ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለመፍታት ይቻል ዘንድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

### 1. ጠቅላላ

#### 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የተማሪዎች ቅበላ መመሪያ ቁጥር 004/2010 ዓ.ም. ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

#### 1.2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱት ቃላት ሌላ ትርጉም እስካልተሰጣቸው ድረስ የሚከተሉት ትርጓሜዎች ተሰጥቷቸዋል፡፡

1.1.1. **ትምህርት ቤት ማለት፡** ከቅድመ መደበኛ እስከ መሰናዶ ለሚማሩ ተማሪዎች የቀለም ትምህርት የሚሰጥባቸው ተቋማት ናቸው፡፡

1.1.2. **ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ማለት፡** ዕድሜያቸው ከሦስት ዓመት ተኩል ጀምሮ ያሉ ሕጻናት ለሦስት ተከታታይ የትምህርት ዘመናት ለመደበኛ ትምህርት ተገቢ ዝግጅት የሚያደርጉበት ትምህርት ቤት ነው፡፡

1.1.3. **ጀማሪ ("0") ክፍል ማለት፡** ዕድሜያቸው ከአምስት እስከ ስድስት ዓመት ሆኖ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ያልቻሉ ሕጻናትን በአንድ ዓመት የቆይታ ጊዜ ለመደበኛ ትምህርት ለማዘጋጀት በመንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚከፈት ክፍል ነው፡፡

1.1.4. **አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማለት ፡** ዕድሜያቸው ዐሥራ ዐራት ዓመት እና በታች ሆኖ በትክክለኛ የተማሪዎች የቅበላ ዕድሜ(ሰባት ዓመት ጀምሮ) ወደ መደበኛ ትምህርት መርሐ ግብር ገብተው መማር ላልቻሉ ሕጻናት መሠረታዊ ትምህርት በአማራጭነት የሚሰጥበት ስልት ነው፡፡

1.1.5. **የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ማለት ፡** ዕድሜያቸው ከዐሥራ አምስት እስከ ስድሳ ዓመት ሆኖ መሠረታዊ ትምህርት ያላገኙ ጎልማሶች ለሁለት የትምህርት ዘመናት መሠረታዊ ትምህርትና የሙያ ክህሎት የሚማሩበት የትምህርት መርሐ ግብር ነው፡፡

1.1.6. **አንድ የትምህርት ዘመን ማለት ፡** ከቅድመ መደበኛ እስከ መሰናዶ ለሚማሩ ተማሪዎች የቀለም ትምህርት የሚሰጥባቸው ከነሐሴ መጨረሻ ሳምንት እስከ ሰኔ 30 ያሉት ወራት ናቸው፡፡



CamScanner

1.1.7. የትምህርት ቤት መክፈቻ ቀን ማለት ፡ ከቅድመ መደበኛ እስከ መሰናዶ ለሚማሩ ተማሪዎች የቀለም ትምህርት ለመስጠት ዝግጅት የሚደረግበት የነሐሴ ወር መጨረሻ ሳምንት ነው፡፡

1.1.8. የትምህርት ቤት መዝጊያ ቀን ማለት ፡ አንድ የትምህርት ዘመን የሚጠናቀቅበት የሰኔ ወር የመጨረሻ ሳምንት ነው፡፡

1.1.9. የተማሪ ቅበላ ማለት ፡ ተማሪዎች ወደ አንድ ትምህርት ቤት ገብተው ለመማር እንዲችሉ የሚከናወን የምዝገባ ሂደት ነው፡፡

1.1.10. የተማሪዎች ቅበላ ጊዜ ማለት፡ በየዓመቱ ከሐምሌ እስከ ነሐሴ መጨረሻ ባሉት ወራት ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን የተማሪዎች ምዝገባ የሚከናወንበት ጊዜ ነው፡፡

1.1.11. የተማሪዎች ቅበላ መጠን ማለት ፡ አንድ ትምህርት ቤት በአንድ የትምህርት ዘመን በአንድ የክፍል ደረጃ ሊያስተናግድ የሚችለው የተማሪ ብዛት ነው፡፡

1.1.12. የተማሪዎች ትክክለኛ የቅበላ ዕድሜ(official school age) ማለት ፡ ተማሪዎች በተገቢ ዕድሜያቸው ትምህርት ቤት የሚገቡበት ጊዜ ነው፡፡

1.1.13. የተማሪዎች ቅበላ መስፈርት ማለት፡ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ለመግባት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡

1.1.14. ደጋሚ ተማሪዎች ማለት ፡ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ዘመን ከተማሩት ትምህርት የሚጠበቅባቸውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ተመዝነው አጥጋቢ ውጤት ባለማስመዝገባቸው ምክንያት በቀጣይ የትምህርት ዘመን የደረጃውን ትምህርት ደግመው እንዲማሩ የሚደረጉ ተማሪዎች ናቸው፡፡

1.2.15. አቋራጭ ተማሪዎች ማለት ፡ በአንድ የትምህርት ዘመን በአንድ ትምህርት ቤት በአንድ የክፍል ደረጃ ለመማር ተመዝግበው የትምህርት ዘመኑ ሳይጠናቀቅ በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ያቋረጡ ተማሪዎች ናቸው፡፡

1.1.16. የዳግም የተማሪዎች ቅበላ ማለት ፡ በአንድ የትምህርት ዘመን በአንድ ክፍል ሲማሩ ቆይተው አጥጋቢ ውጤት ባለማምጣታቸው ወይንም በተለያየ ምክንያት ትምህርታቸውን አቋርጠው የወጡ ተማሪዎች በቀጣዩ የትምህርት ዘመን ገብተው እንዲማሩ የሚመዘገቡበት ሥርዐት ነው፡፡

1.1.17. የተማሪዎች ዝውውር ማለት ፡ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ዘመን አጋማሽ ወይንም መጨረሻ ከአንድ ትምህርት ቤት ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ተዘዋውረው መማር የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚከናወን የአሠራር ሥርዐት ነው፡፡

1.1.18. የመርሐ ግብር ሽግግር ማለት ፡ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ዘመን አጋማሽ ወይንም መጨረሻ ከአንድ የትምህርት መርሐ ግብር ወደ ሌላ ትምህርት መርሐ ግብር



Government of Addis
EDUCATION BUREAU

CamScanner

ተዘዋውረው መማር የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚከናወን የአሠራር ሥርዓት ነው፡፡

1.1.19. የትምህርት ማስረጃ ፡ ተማሪዎች በአንድ ትምህርት ቤት በአንድ የትምህርት ዘመን በአንድ የክፍል ደረጃ ወይንም በአንድ የትምህርት እርከን ተመዝግበው በመማር ላስመዘገቡት ውጤት የሚሰጥ ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡

1.1.20. ወላጅ/ አሳዳጊ ፡ የአንድ ተማሪ አባት/ እናት ወይንም ለማሳደግ ሕጋዊ መብት የተሰጠው ግለሰብ ነው፡፡

1.1.21. የኅብረተሰብ ተሳትፎ ፡ የተማሪዎች ወላጆች/ አሳዳጊዎች ወይም የአካባበው ኅብረተሰብ ለትምህርት ቤት ምቹ የመማሪያ አካባቢ ለመፍጠር በገንዘብ፣ በጉልበት፣ በእውቀት እና ለትምህርት አስፈላጊ በሆኑ ቁሳቁሶች የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ነው፡፡

## 1.2. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ በሚገኙ የመንግሥት፣ የግልና መንግሥታዊ ባልሆኑ የቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 2. በተማሪዎች ቅበላ የወላጅ/የኅብረተሰብ/ መብትና ግዴታዎች

2.1. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱትን ሕጻናት ወደ ትምህርት ቤት የመላክ ግዴታ አለባቸው፡፡

2.2. ወላጆች ልጆቻቸውን ወይም የሚያሳድጓቸውን ሕጻናት ወደ መንግሥት ትምህርት ቤት በሚልኩበት ወቅት እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ምንም ዓይነት የምዝገባ ክፍያ አይጠየቁም፡፡

2.3. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ልጆቻቸው ለሚማሩበት ትምህርት ቤት አቅማቸው በፈቀደ መጠን በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በጉልበት፣ በሐሳብና በሙያው ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡ነገር ግን እነዚህ ድጋፎች በተማሪዎች ምዝገባ ወቅት እና ተማሪዎች ሪፖርት ካርድ እና መልቀቂያ በሚወስዱበት ወቅት በአስገዳጅነት መከናወን አይኖርበትም፡፡

2.4. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ወይም በአካባቢው የሚገኙ የማህበረሰብ አባላት በሚገኙበት ወረዳ ውስጥ ዕድሜያቸው ለትምህርት ደርሶ ትምህርት ቤት ያልገቡና በልዩ ልዩ ምክንያት ተደብቀው ትምህርት ያላገኙ ሕጻናትን በመለየት ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ ለትምህርት ቤቱ መረጃ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡



CamScanner

2.5. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች ትምህርት ቤቱ ከሚገኝበት ከወረዳው ኅብረተሰብ ጋር በትምህርት ልማት ቀጥተኛ ግንኙነት በመፍጠር በጋራ የመሥራት ግዴታ አለባቸው፡፡

2.6. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች በትምህርት ቤት ስለሚያስመዘግቧቸው ሕጻናት አካላዊ፣ አእምሮአዊና ሌሎች የጤና ሁኔታዎች ተገቢ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

2.7. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች በትምህርት ቤት የሚያስመዘግቧቸውን ሕጻናት የልደት የምሥክር ወረቀትና የክትባት ወረቀት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

2.8. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች በትምህርት ቤት ለሚያስመዘግቧቸው ሕጻናት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ኃላፊነት መውሰዳቸውን በተማሪዎች ምዝገባ ወቅት በፊርማቸው የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፡፡

2.9. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች በትምህርት ቤት ለሚያስተምሯቸው ሕጻናት የትምህርት አቀባበልና የሥነ ምግባር ሁኔታ ከትምህርት ቤቱ ጋር ተከታታይነት ያለው ግንኙነት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

2.10. ወላጆች ወይንም አሳዳጊዎች በትምህርት ቤት ስለሚያስተምሯቸው ሕጻናት ጉዳዮች በተመለከተ በተጠሩ ጊዜ በአካል ወደ ትምህርት ቤት ቀርበው የመነጋገር ግዴታ አለባቸው፡፡

## ክፍል ሶስት

3. ለተማሪዎች ምዝገባ የሚያስፈልጉ ሂደቶች

3.1. አዲስ ተማሪዎችን በትምህርት ቤት የሚያስመዘግቡ ወላጆች/ አሳዳጊዎች/ ልጃቸው/ጆቻቸውን በትምህርት ቤቱ ለማስመዝገብ ጥያቄያቸውን በጽሑፍ ያቀርባሉ፡፡

3.2. ትምህርት ቤቱ በጽሑፍ በቀረበው ጥያቄ መሠረት ተማሪውን ይመዘግባል፡፡ ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያት ተማሪውን የማይቀበል ከሆነ እጅግ ቢዘገይ በአንድ ቀን ውስጥ በጽሑፍ ምላሽ ይሰጣል፡፡

3.3. ወላጆች/ አሳዳጊዎች ከላይ በተጠቀሰው ቀን ውስጥ ጥያቄያቸው ካልተመለሰላቸው ጥያቄያቸውንና ከትምህርት ቤቱ የተሰጣቸው ምላሽ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሆነ ለወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት 2ኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ቤት ከሆነ ለክፍለ ከተማው ትምህርት ጽ/ቤት አያይዘው ያቀርባሉ፡፡ የወረዳው/ የክፍለ ከተማው ትምህርት ጽ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ በአንድ ቀን ውስጥ ምላሹን በጽሑፍ ለወላጅ ይሰጣል፡፡

3.4. በሐሰተኛ ወይንም በተጭበረበረ የትምህርት ማስረጃ የተመዘገበ ተማሪ ወይንም ልጁን ወይም የሚያሳድገውን ተማሪ ያስመዘገበ ወላጅ ወይም አሳዳጊ በተጨባጭ ማስረጃ ከተያዘ ተማሪው በተመዘገበበት ክፍል ያገኘው የትምህርት ውጤት ሙሉ በሙሉ ከመሰረዙ በተጨማሪ ተማሪው ወይም አስመዝጋቢው በአካባቢው ለሚገኝ የሕግ አካል ተላልፎ ይሰጣል።

3.5. ወላጆች/ አሳዳጊዎች በትምህርት ቤት ልጆቻቸውን ሲያስመዘግቡ በትምህርት ቤቱ የሚጠየቁትን ለምዝገባ አስፈላጊ ሰነዶች አያይዘው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

3.6. ትምህርት ቤቶች በምዝገባ ወቅት ወይንም ከሌላ ትምህርት ቤት በዝውውር ለሚመጡ የተማሪ ወላጆች ስለ ትምህርት ቤቱ ደንብ፣ ስለ ሥርዓተ ትምህርቱ፣ ስለ ትምህርት ዘመኑና ስለ ፈተና አሰጣጥ ሥርዓቱ በዝርዝር የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

3.7. ትምህርት ቤቶች በምዝገባ ወቅት አዲስ ለሚቀበሏቸው ተማሪዎች ተጨማሪ እገዛ ወይንም ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን ካረጋገጡ ለወላጆች የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ክፍል አራት

### 4.1. የዜጎች የተጠቃሚነት መብት

4.1.1. ሁሉም ዜጎች በተለያዩ የትምህርት መርሐ ግብር የትምህርት አገልግሎት ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡

4.1.2. በከተማችን የሚገኙ ዜጎች በብሔር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በጾታና በምጣኔ ሀብት አቅም እና በአካላዊ ጉዳት ልዩነት ሳይደረግባቸው በከተማው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በማንኛውም የትምህርት መርሐ ግብር ገብተው የመማር መብት አላቸው፡፡

### 4.2. ልዩ ፍላጎትና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎችን በተመለከተ

4.2.1. ትምህርት ቤቶች በቅበላ ወቅት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው ዓይነት በአግባቡ የመለየትና መረጃ የመያዝ ግዴታ አለባቸው፡፡

4.2.2. ትምህርት ቤቶች እስከ አምስተኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነት ዘጠና አምስት በመቶና ከዚያ በላይ ያስመዘገቡ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች እንደ ፍላጎታቸው በአንድ ዓመት ሁለት ጊዜ ከክፍል ወደ ክፍል ማዘዋወር ይችላሉ፡፡

4.2.3. ትምህርት ቤቶች በሁሉም መርሃ ግብሮች ለሚማሩ ተማሪዎች በተለዩ የትምህርት ዓይነቶች (በሂሳብና በሳይንስ) ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት የተለየ ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## ክፍል አምስት

### 5. የትምህርት ቤቶች ግዴታ

#### 5.1.አጠቃላይ ግዴታዎች

5.1.1. የመንግሥት ትምህርት ቤቶች በሚገኙበት ወረዳ/ ኩታገጠም ወረዳዎች/ ውስጥ ለሚኖሩ የኅብረተሰብ ልጆች የመደበኛ ትምህርት የመስጠት እንዲሁም ለኅብረተሰቡ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትና በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት በጣቢያነት የማገልገል እና የትምህርት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

5.1.2. ትምህርት ቤቶች ለኅብረተሰቡ የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት የቅድመ መደበኛና የመደበኛ ትምህርት የተማሪዎችን ቅበላ በዚህ መመሪያ መሠረት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተቀብሎ ማስተማር አለባቸው፡፡

5.1.3. የመንግሥት ትምህርት ቤቶች በተለያዩ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ችግሮች ምክንያት በመደበኛ ትምህርት መማር ላልቻሉ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተማሪዎች በሚመርጡት የትምህርት ሰዓት እንዲማሩ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለባቸው፡፡

5.1.4. የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ለማታ፣ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት እና ለተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትተማሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል የመጻሕፍት አቅርቦት፣ የቁሳቁስና የመማር ማስተማር ሂደቱን የመከታተልና ድጋፍ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

5.1.5. ሁሉም የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ከወላጆች ጋር ቀጥተኛና መደበኛ ግንኙነት በመፍጠር በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ዕድሚያቸው ለቅድመ መደበኛና ለመደበኛ ትምህርት የደረሱ ሕጻናትን መረጃ መዝግቦ የመያዝና የትምህርት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡

5.1.6. ማንኛውም ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ብቻ ያለው እንዲሁም የቅደመ መደበኛና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትን በአንድ ላይ አጠቃሎ የያዘ የመንግስት ትምህርት ቤት በአካባቢው የሚገኙ ሕጻናትን በፍራ በማመቻቸት ተቀብሎ የማስተማር ግዴታ አለበት፡፡



CamScanner

5.1.7. ወረዳውና ትምህርት ቤቶች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕጻናትን በመለየትና ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ የቅድሚያ ትኩረት ማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

5.1.8 እያንዳንዱ ወረዳ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕጻናትን በመለየት የቅድመ መደበኛ ትምህርት እንዲያገኙ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

5.1.9. እያንዳንዱ ወረዳ የቅድመ መደበኛ ትምህርት እድል ያላገኙና የመማሪያ ዕድሜያቸው ያለፈባቸው (ከ5 እስከ 6 ዓመት) የሆኑ ሕጻናትን በወረዳው ሥር በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀማሪ ክፍል (O class) በመክፈት የማስተማር ግዴታ አለበት፡፡

5.1.10. ወረዳው ትምህርት ቤቶች የሚቀበሏቸውን ሕጻናት መረጃ ማለትም የልደት የምስክር ወረቀት የክትባት ካርድ እንዲሁም ሕጻናት በየጊዜው የሚያመጡትን አካላዊና አእምሯዊ ለውጦችን በተመለከተ የተሟላ መረጃ እንዲይዙ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

5.1.11. ተማሪዎች ከአንድ ትምህርት ቤት ሲለቁ ወይንም ሲዛወሩ ለተቀባዩ ትምህርት ቤት የትምህርት አቀባበላቸውን፣ የሥነ ምግባር ሁኔታቸውንና ሌሎች ጉዳዮችን በጽሑፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

5.1.12. በሁሉም የመንግሥት፣ የግልና መንግሥታዊ ባልሆኑ የትምህርት እርከን የተማሪዎች ቅበላ የተማሪዎችን የትምህርት ብቃት መሠረት ያደረገ መሆን የለበትም፡፡

5.1.13. ከቅድመ መደበኛ እስከ 0ሥረኛ ክፍል ባሉ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ትምህርት የሚሰጠው በነጻ በመሆኑ ለተማሪዎች ቅበላ የመመዝገቢያ ክፍያ አይጠየቅም፡፡

## 5.2. በቅድመ መደበኛ ትምህርት

5.2.1. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤትና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀማሪ ክፍል (O class) የሚማሩ ሕጻናት ምዝገባ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 15 ባሉት ቀናት ይከናወናል፡፡

5.2.2. ሁሉም ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕጻናት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ገብተው የመማር መብት አላቸው፡፡

5.2.3. ዕድሜያቸው ከአምስት እስከ ስድስት ዓመት የሆኑና በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ያልቻሉ ሕጻናት ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት

በጀማሪ ክፍል (O class) ገብተው ለአንድ ዓመት መሠረታዊ የንባብና የጽሑፍ ክህሎት የመማርና በቀጥታ ወደ አንደኛ ክፍል የመመዝገብ መብት አላቸው፡፡

5.2.4. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤትና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀማሪ ክፍል (O class) የሚመዘገቡ ሕጻናት ለአካላዊ፣ ለአእምሮአዊና ለማኅበራዊ ዕድገታቸው ምቹ፣ ጤንነቱ በተጠበቀና ለደኅንነታቸው በማያሰጋ አካባቢ የመማር መብት አላቸው፡፡

5.2.5. በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት የሚማሩ ሕጻናት በትምህርት ቤት ቆይታቸው ለአደጋ እንዳይጋለጡ የሚንከባከቧቸውና የሚጠብቋቸው ሞግዚቶች የማግኘት መብት አላቸው፡፡

5.2.6. የአካል ጉዳት ወይንም የልዩ ትምህርት ፍላጎት ያላቸው ሕጻናት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤትና በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀማሪ ክፍል(O class) ተገቢ ትኩረትና እንክብካቤ በማግኘት የመማር መብት አላቸው፡፡

## 5.3. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት

5.3.1. የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ቤቶች የተማሪዎችን አሰፋፈርና የትምህርት ቤት መገኛ ካርታ (school map) መሠረት ያደረገ የቅድመ መደበኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ከክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኅብረተሰቡን ጥያቄ የመፍታት ግዴታ አለባቸው፡፡

5.3.2. እያንዳንዱ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕጻናትን በወረዳው ውስጥ ካለው የኅብረተሰብ ክፍል በመለየት የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ግዴታ አለበት፡፡

5.3.3. እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ዕድሜያቸው ከስድስት ዓመት በላይ የሆናቸውና ቅድመ መደበኛ ትምህርትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጀማሪ ክፍል (O class) የተማሩ ሕጻናትን በሙሉ ለአንደኛ ክፍል ተቀብሎ እንዲማሩ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

## 5.4. የሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት

5.4.1. የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች የተማሪዎችን አሰፋፈር፣ የመጋቢ ትምህርት ቤቶች ሁኔታና የትምህርት ቤት መገኛ ካርታ (school map) መሠረት ያደረገ የሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ከቢሮ ጋር በመተባበር የኅብረተሰቡን ጥያቄ የመፍታት ግዴታ አለባቸው፡፡

5.4.2. ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎችን ወረዳና ክፍለ ከተማ ሳይለዩ የሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርታቸውን በሚቀርባቸው አካባቢ መማር እንዲችሉ የመቀበል ግዴታ አለባቸው፡፡

5.4.3. ከሌሎች ክልሎች የሚመጡ ተማሪች በሚቀርባቸው ክፍለ ከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች መማር እንዲችሉ ክፍለ ከተማ እና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች አሰራር በመዘርጋት ተማሪዎችን መቀበል ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 5.5. አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ቅበላ፣ ዝውውር እና ሽግግር

5.5.1.መደበኛ ትምህርት መከታተል የማይችሉ ዕድሚያቸው ከ7-14 ዓመት የሆኑ ሕጻናት በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተመዝግበው የመማር መብት አላቸው፡፡

5.5.2.የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የሚያስተምሩ ተቋማት ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተማሪዎች የተዘጋጀውን ሥርዓተ ትምህርት ተከትለው የማስተማር ግዴታ አለባቸው፡፡

5.5.3. የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የሚያስተምሩ ተቋማት በመርሐ ግብሩ ትምህርት ተከታትለው ላጠናቀቁ ተማሪዎች የማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መስጠት አለባቸው፡፡

5.5.4 በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብር ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች በሽግግር መመሪያው መሰረት ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ይችላሉ፡፡

5.5.5. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አጠናቀው በፍላጎታቸው ለሚመጡና የማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት የሚያቀርቡ ተማሪዎችን በሽግግር መመሪያው መሰረት ተቀብለው በመደበኛ ትምህርት መዝግበው የማስተማር ግዴታ አለባቸው፡፡

5.5.6. የሽግግር መመሪያው በግልጽ ያላስቀመጣቸው ጉዳዮች ካሉ የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች ከትምህርት ቢሮ ጋር በመነጋገር የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፡፡

5.5.7. ትምህርት ቤቶችና የትምህርት ቤት አመራሮች ትምህርት ቤቱን ለአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሐ ግብር ክፍት የማድረግ፣ መርሐ ግብሩን በሥርዐት የመምራትና በተገቢ ግብዓት መደገፍ አለባቸው፡፡

## 6. የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ቅበላ፣ ዝውውር እና ሽግግር

5.6.1. ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 60 ዓመት የሆኑ ጎልማሶች በተቀናጀ ተግባር ተኮር ጎልማሶች ትምህርት መርሐ ግብር የመማር መብት አላቸው።

5.6.2. እያንዳንዱ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ከማኅበረሰቡ ውስጥ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን የመለየት፣ የመመዝገብና መረጃውን የማደራጀት ግዴታ አለበት።

5.6.3. እያንዳንዱ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ለተቀናጀ የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሥልጠና ማዕከሎችን የመክፈት፣ ግብዓት የማሟላት፣ ጎልማሶችን የመቀበልና ለውጤታማነቱ ባለድርሻ አካላትን የማስተባበርና የመምራት ግዴታ አለበት፡፡

5.6.4. በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሚሳተፉ ጎልማሶች ለደረጃው የተቀመጠውን ሥርዓተ ትምህርት ሲያጠናቅቁ የሚረጋገጥ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ፡፡

5.6.5. የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የሚሰጡ ማዕከሎች ትምህርታቸውን ላጠናቀቁ ጎልማሶች የሚረጋገጥ የምስክር ወረቀት መስጠት አለባቸው፡፡

5.6.6. በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መርሐ ግብር የሚሰጠውን ትምህርት ተምረው ያጠናቀቁ ጎልማሶች እንደፍላጎታቸው በሽግግር መመሪያው መሰረት ወደ መደበኛ ትምህርት ገብተው መማር ይችላሉ፡፡

5.6.7. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መርሐ ግብር የሚሰጠውን ትምህርት ተምረው ያጠናቀቁ ጎልማሶችን በሽግግር መመሪያው መሰረት ተቀብለው ማስተማር አለባቸው፡፡

5.6.8. የሽግግር መመሪያው በግልጽ ያላስቀመጣቸው ጉዳዮች ካሉ የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች ከትምህርት ቢሮ ጋር በመነጋገር የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፡፡

5.6.9. ማንኛውም የመንግስት ትምህርት ቤትና የትምህርት ቤት አመራር ትምህርት ቤቱን ለተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መርሐ ግብር ክፍት የማድረግ፣ ጎልማሶችን የመቀበልና መርሐ ግብሩን የመምራትና በተገቢው ግብዓት የመደገፍ ግዴታ አለበት፡፡

## 5.7. የማታ ተከታታይ ትምህርት ቅበላ፣ዝውውር እና ሽግግር

5.7.1. ትምህርታቸውን በቀን መደበኛ መርሐ ግብር መከታተል የማይችሉ ዜጎች በማታ ትምህርት መርሐ ግብር መማር ይችላሉ፡፡

5.7.2. የማታ ተከታታይ ትምህርት ተከታትለው ለደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች በመረጡት መርሐሃ ግብር በቀን ወይንም በርቀት ትምህርት የመማር መብት አላቸው፡፡

5.7.3. ትምህርት ቤቶችም በማታ መርሐ ግብር ተምረው ወደ ቀን መርሐ ግብር ለመዘዋወር የሚጠይቁ ተማሪዎችን በትምህርት ማስረጃቸው መሠረት ተቀብለው የማስተማር ግዴታ አለባቸው፡፡

5.7.4. በማታ ትምህርት መርሐ ግብር ከዘጠነኛ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል የሚሰጠው የእያንዳንዱ ክፍል ትምህርት የሚጠናቀቀው በሦስት መንፈቀ ዓመት ነው፡፡

5.7.5. በማታ ሲማሩ የቆዩ ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ያሉ ተማሪዎች ወደ ቀን ትምህርት መርሐ ግብር ለመዘዋወር ሲፈልጉ የሦስት መንፈቀ ዓመት ትምህርት ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

5.7.6. ትምህርት ቤቶች የማታ ትምህርት መርሐ ግብር ሲያካሂዱ ለትምህርቱ በቂ ግብዓት ማሟላትና መምህራንን በሥራ ባህሪያቸው በሙያ ብቃታቸው መመደብ አለባቸው፡፡

## 5.8. የርቀት ትምህርት መርሐ ግብር ቅበላ፣ዝውውር እና ሽግግር

5.8.1. ዕውቅና ባላቸው የርቀት ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን ያጠናቀቁና ለደረጃው ብቁ መሆናቸው የተረጋገጠላቸው ተማሪዎች በቀን ወይንም በማታ መደበኛ ትምህርት የመማር መብት አላቸው፡፡ ትምህርት ቤቶችም እነዚህን ተማሪዎች ተቀብለው የማስተማር ግዴታ አለባቸው፡፡

5.8.2. የርቀት ትምህርት የሚያስተምሩ ተቋማት ተማሪዎችን ተቀብለው ለማስተማር አስፈላጊውን ግብዓት በማሟላት ከሚመለከተው አካል እውቅና ሊኖራቸው ይገባል፡፡

5.8.3. የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች እውቅና ፍቃድ ያላቸውን ትምህርት ቤቶች ዝርዝር በስሩ ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

5.8.4. እውቅና የተሰጣቸው የርቀት ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችን ሲቀበሉ ተማሪዎቹ ሕጋዊ የትምህርት ማስረጃ ያላቸው መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው።

ክፍል ስድስት

## 6. የተማሪዎች የትምህርት ማስረጃ አሰጣጥ

6.1. የትምህርት ተቋማት በማንኛውም የትምህርት መርሐ ግብር ትምህርታቸውን ሳጠናቀቁ ተማሪዎች ሳጠናቀቁበት የትምህርት ደረጃ ማስረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

6.2. ለዓመቱ የተመደበውን ትምህርት ያላጠናቀቁ ተማሪዎች የሚሰጣቸው መረጃ ቢያንስ የአንድ መንፈቀ ዓመት ውጤት መያዝ አለበት።

6.3. በአስገዳጅ ሁኔታ የአንድ መንፈቀ ዓመት ትምህርት ሳያጠናቅቁ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ተማሪዎች ሲያጋጥሙ የክፍለ ከተማው ትምህርት ጽ/ቤት አስፈላጊውን ውሳኔ ያስተላልፋል።

6.4. ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች በዓመቱ መጨረሻ ወይም በመንፈቀ ዓመት መጨረሻ ላይ መስጠት የሚችሉት የምስክር ወረቀት(Certificate) ብቻ ነው።

6.5. የሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም የመሰናዶ ትምህርታቸውን ሳጠናቀቁ ተማሪዎች ከምሥክር ወረቀት በተጨማሪ አጠቃላይ የውጤት መግለጫ(transcript) ይሰጣቸዋል።

6.6. በሁሉም ትምህርት ቤቶች የሚሰጠው የተማሪዎች የምስክር ወረቀት(Certificate) እንዲሁም አጠቃላይ የውጤት መግለጫ(transcript) የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይጠበቅበታል።

6.6.1.በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ የ____________ ትምህርት ቤት የተማሪዎች የምስክር ወረቀት(Certificate) አጠቃላይ የውጤት መግለጫ(transcript)

6.6.2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የትምህርት ቤቱ ዓርማ

6.6.3.የትምህርት ቤቱ ሙሉ አድራሻ

6.6.4.የተማሪው ሙሉ ስም

6.6.5.የተማሪው የልደት ቀን፣ ፆታ

6.6.6.ተማሪው በየትምህርት ዓይነቱ ያስመዘገበው ውጤት እና የቀረበት ቀን ብዛት

6.6.7.ተማሪው ያጠናቀቀው የክፍል ደረጃ

6.6.8. ተማሪው ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ማለፍ ወይንም አለማለፉን እንዲሁም በአጠቃላይ የውጤት መግለጫ(transcript) ላይ የሁለተኛ ደረጃ ወይንም የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ ማጠናቀቁን መግለጫ

6.6.9. የክፍል መምህሩ ስምና ፊርማ ( በተማሪዎች የምሥክር ወረቀት ላይ ብቻ)

6.6.10. የተማሪዎች ሪከርድና መዝክር ኃላፊ ፊርማ (የተማሪዎች ትራንስክሪፕት ላይ ብቻ)

6.6.11. የርዕሰ መምህሩ ስማና ፊርማ

6.7. ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ ትምህርት ቤት ለሚለቁ ተማሪዎች በወላጆቻቸው ወይም በአሳዳጊያቸው ጥያቄ መሠረት ብቻ የመልቀቂያ ወረቀት የመውሰድ መብት አላቸው።

6.7.1.ለተማሪዎች የሚሰጠው የመልቀቂያ ወረቀት ተማሪዎቹ የሚገቡበትን ትምህርት ቤት መጥቀስ አለበት።

6.7.2. ትምህርታቸውን መቀጠል የማይፈልጉ ተማሪዎች ሔደው የሚመዘገቡበት ትምህርት ቤት ሰረዝ ተደርጎ ይሰጣቸዋል፣ ለመማርም በፈለጉ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤታቸው ተመልሰው ሄደው የሚቀበላቸውን ትምህርት ቤት ስም የመልቀቂያ ወረቀት ላይ ማጻፍ አለባቸው።

6.7.3. ትምህርት ቤቶች ከሌላ ትምህርት ቤት የመጡ ተማሪዎችን የሚቀበሉት ተማሪዎቹ ይዘው የሚመጡት የመልቀቂያ ወረቀት የተሟላ መረጃ መያዙን ሲያረጋግጡ ብቻ ነው።

## ክፍል ሰባት

## 7. ከስደት ተመላሾች ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንንና ሌሎችን በተመለከተ

7.1. የየመን እና የኤርትራ ስደተኞች የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር ስደተኞችን እና ከስደት ተመላሾችን ለማስተናገድ ባወጣው መመሪያ ይስተናገዳሉ።

7.2. ከኤርትራ እና ከየመን ውጪ ያሉ ከስደት ተመላሾች ኢትዮጵያውያን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ሌሎችን በትምህርት ቤት ለመመዝገብ የሚፈልጉ ሁሉ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመለከተው ክፍል ስደተኛ ስለመሆናቸው የማረጋገጫ ደብዳቤ

በማቅረብ የኢ.ፌዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር ለኤርትራ እና ለየመን ስደተኛ እና ከስደት ተመላሾች ባወጣው መመሪያ መስተናገድ ይችላሉ።

7.3. የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች ስደተኛ እና ከስደተኛ ተመላሽ ዜጎችን የኢ.ፌዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ የማስተናገድ ግዴታ አለባቸው።

7.4. የኢ.ፌዲ.ሪ የትምህርት ሚኒስቴር ያወጣው መመሪያ በግልጽ ያላስቀመጣቸው ጉዳዮች ካሉ የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች ከትምህርት ቢሮ ጋር በመነጋገር የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ።

## ክፍል ስምንት

### 8. ትምህርት አቋርጠው መማር የሚፈልጉ ተማሪዎች ቅበላ

8.1. በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ያቋረጡ ዜጎች ሥርዓተ ትምህርቱ እስካልተቀየረ ድረስ ካቋረጡበት ክፍል ጀምረው መማር ይችላሉ፡፡

8.2. በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርታቸውን ያቋረጡ ዜጎች ወደ ትምህርታቸው ለመመለስ በጠየቁ ጊዜ ሥርዓተ ትምህርቱ የተቀየረ እንደሆነ ትምህርት ሚኒስቴር በሚያወጣው የሽግግር መመሪያ መሰረት ይስተናገዳሉ፡፡

8.3. ተማሪዎች አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ እና የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ብሔራዊ ፈተና አለመውሰዳቸውን ሲማሩበት የነበረው ትምህርት ቤት ካረጋገጠ ተመዝግበው መማር ይችላሉ፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

### 9. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9.1. መመሪያውን ስለማሻሻል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ይህንን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ይችላል።

9.2. ስለ ተሻሩ መመሪያዎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረኑ ወይንም የሚጥሱ ከዚህ በፊት የነበሩ መመሪያዎች በሙሉ በዚህ መመሪያ መሠረት ተሽረዋል።

9.3. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

9.4. **መመሪያ ስለመተላለፍ**

በዚህ መመሪያ ላይ የተዘረዘሩትን ተግባራት ያልተገበረ ወይንም የተላለፈ በወንጀል ከመጠየቁም በተጨማሪ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስ አዋጅ ቁጥር 6/2000 መሠረት በዲስፕሊን ይጠይቃል።

ታቦር ገብረመድህን(ዶ/ር)

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ

